# Finote Ethio-Canadian Information Centre In Toronto
## ፍኖተ ኢትዮ-ካናዳውያን የኢንፎርሜሽን ማዕከል በቶሮንቶ
1910 Kennedy Road, Unit 3,   P.O.Box 417, Toronto, ON, M1P 2L8    E-mail: torontofinote@gmail.com


## ከትውልድ ትውልድ ሕዝብ በከፈለው መስዋዕትነት ኢትዮጵያ ተጠብቃ ትኖራለች!

ኢትዮጵያ በታሪኳ ብዙ ፈተናዎችን ተፈትና፣ ብዙ ችግሮችን ተቋቁማ እንደ ሀገር ለመቀጠል ያቻለችው በታላቅ ሕዝቧ ተጋድሎና መስዋዕትነት፣ በመልካም፣ ጀግና፣ ቆራጥና ብልህ መሪዎቿ አመራር ነው፡፡ የሕዝቧዋ ተጋድሎ ሲባል፤ ክቡር ህይወቱን ሰውቶ፣ ደሙን አፍስሶ፣ አጥንቱን ከስክሶ፣ አካለ ጎደሎ ሆኖ፣ ተሰዶና ተሰቃይቶ የተከፈለ መሆኑን ታሪክ ይነግረናል፡፡ ኢትዮጵያ ችግሮች የገጠሟትና የሚገጥሟት አንድም ከውስጥ በሚነሳ የስልጣን ሽኩቻ ወይም በሃይማኖት ጦርነት ስበብ ሲሆን ሌላም በውጭ ወራሪ ቅኝ ገዢዎች የመጣ የባዕድ ወረራ ነበር፡፡

ኢትዮጵያን በአለም ዙሪያ ያስጠሩ ታላላቅ ነገስታቶች የነገሱባት፣ በሃይማኖት፣ በስነ ጽሁፍ፣ በፍልስፍና፣ በንግድ ግንኙነት እና አልነካ ባይነት ዝናዋ የገነነበት ዘመናትን አሳልፋለች፡፡ ፈተናና ጥፋት ሲገጥማት፤ ለአብነት ያህል ለመጥቀስ በሃይማኖት ስበብ በዮዲት ጉዲት ዘመን ብዙ ጥፋቶች እንደጠፉ፣ ብዙ ክርስቲያን ሕዝብም እንዳለቀ ይታወቃል፡፡ ሌላም በግራኝ አህመድ ዘመን ደግሞ እንደዚሁ ለ 19 ዓመታት ያህል በሃይማኖት ሰበብ ብዙ ሕዝብ ያለቀበት፣ ብዙ ቤተክርስቲያኖች የተቃጠሉበት፣ የቤተክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት፣ የታሪክ መዛግብት፣ የሀገር ቀርስ የወደሙበት የጥፋት ዘመን ነበር፡፡ የኢትዮጵያ መንግስትም ታሪክን ሊለውጥ በሚችል ደረጃ የተዳከመበት፣ ያንንም ተከትሎ ከደቡብ ኢትዮጵያ ወደ መሃልና ስሜን ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነ የኦሮሞ ነገድ ፍልሰትና መስፋፋት ተካሂዶ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ተጽዕኖ ያሳደረ ታሪክ የተቀየረበት ዘመን እንደነበር ታሪክ ያስረዳል፡፡ በዚያም የተነሳ ማዕከላዊ መንግስት ተዳክሞ ዘመነ መሳፍንት የተባለው ሰፍኖ ኢትዮጵያ እጅግ ወደኋላ የተጓዘችበት፣  ከሌላው አለም ተለይታ የተረሳችበትም የጭለማ ዘመን  ነበር፡፡

**ኢትዮጵያን ከተዳከመችበት ያነሱዋትና የተጋደሉላት ትውልድና መሪዎች**

በሌላ በኩል፤  ታላላቅ መሪዎች ሲነሱ ደግሞ አንድነቷ ጠንክሮ፣ በአለም ታሪክ ስሟ ገንኖ የምትጠራበት ዘመን መታየት ይጀምራል፡፡ የቅርብ ታሪካችን ከሚያነሳቸው አንዱ አፄ ቴዎድሮስ ተነስተው የጥንት አንድነቷን ለማስመለስ ያደረጉት ተጋድሎ ሌላው የታሪክ ምዕራፍ ነው፡፡ አንድነቷን ገናናነቱዋን ለማስመለስ ትልቅ ሚና፣ ትልቅ ተጋድሎ አድርገው ለውጭ ወራሪ ኃይል እጅ አልሰጥም ብለው የጥንት ያባቶቻቸውን አልነካ ባይነትንና ጀግንነትን ለማሳየት በቆራጥነት ህይወታቸውን የሰዉ ጀግና መሪ ነበሩ፡፡ አፄ ዮሐንስም  ቢሆኑ ከሱዳን በኩል ደርቡሾች እየመጡ ሲያስቸግሩ ከነርሱ ጋር የሀገራቸውን ዳር ደንበር ለማስጠበቅ ሲዋጉ መስዋዕት የሆኑ የኢትዮጵያ መሪ ነበሩ፡፡  ሌላው በኢትዮጵያ ታሪክ በሁሉም መስክ እጅግ የተሳካላቸው ጀግና መሪ ደግሞ ዳግማዊ አጼ ሚኒልክ ሲሆኑ፤ አጼ ሚኒልክ በየትኛውም መመዘኛ ቢሆን ከዘመናቸው ርቀው የመጠቁ ብልህ፣ አስተዋይ፣ ደግ፣ ጀግና መሪ በመሆናቸው በአስተዳደርም ሆነ ኢትዮጵያን ዘመናዊ ለማድረግ እጅግ የደከሙ ከውጭ ወራሪ ጋር ተፋልመው ድፍን ዓለምን ያስደመመ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን አፍሪካን ያኮራ ድል ያደረጉ ጀግና መሪ ነበሩ፡፡ ያ አንጸባራቂ ድል የመጣው ግን የዘመኑ ትወልድ እጅግ ከፍተኛ የሆነ መስዋዕትነት ከፍሎ እንጂ እንደዚሁ በቀላሉ አልነበረም፡፡ ማየትና ማነጻጸር ያለብን በዚያን ጊዜ አውሮፕላን፣ መኪና፣ ታንክም ሆነ ዘመናዊ መጓጓዣ በሌለበት በባዶ እግር ከመቶ ሺህ ሰራዊት በላይ አሰተባብሮና ከመላው ኢትዮጵያ ከፍል ሕዝብ አንቀሳቅሶ፣ ተዋግቶ ድል ማስገኘት እጅግ ከባድ አዳጋችና ውስብስብ ስራ ነበር፡ ፡በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ደማቸውን አፍሠው አጥንታቸውን ከስክሰው አድዋ ላይ አንቀላፍተዋል፡፡ ብዙ ሺዎች አካለ ጎደሎ ሆነው ተመልሰዋል፤ በበሽታ አልቀዋል፣ በአውሬም ተበልተው ቀርተዋል፡፡ እኛን እንድንኮራ ያደረጉን የዚያ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ክብርና ምስጋና ይግባቸውና እነሱ ተሰውተው ለኛ ነጻ አገር አስረክበውናል፡፡ ዛሬ የኢትዮጵያ የውጭ ጠላቶች እንደ እግር እሳት ያሚያንገበግባቸውና ለኢትዮጵያ አልተኛ ያሉት ኢትዮጵያ በአድዋ ድል ያገኘችው የድል ዝና ነው፡፡ ይኸውም እንዴት አንዲት ጥቁር አፈሪካዊት አገር የአውሮፓ አገር ጣሊያንን አሸነፈች በማለት ጥርስ ወስጥ የገባች ስጋ አድርገው ኢትዮጵያን ለማጥፋት እንቅልፍ በማጣት ሲባዝኑ ኢትዮጵያ ለውጭ ወራሪ የማትበገር ሆና በማግኘታቸው የተሻለው የውስጥ ጠላት በመፍጠር ዓላማቸውን ለማሳካት በሀገራችን በነጻ አውጭ ስም እንዲፈጠሩ በማድረግ ሊበቀሉን ከተነሱ በርካታ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡

ሌላው ጠላት የሆነብን ከሀገራችን ፈልቆ ሱዳንን እና ግብጽን የሚያጠጣውና የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ሆኖ የሚያገልግላቸው አባይ ወንዛችን ሲሆን፤ ወሃው በቻ ሳይሆን ለም አፈራችንን ጠራርጎ ይዞ ሄዶ እነርሱን በእርሻ እያለማ ኢትዮጵያ ግን ለበዙ ሺህ ዓመታት ያልተጠቀመችበት (ገና ለኤሌክትሪክ ማመንጫ ሃይል ልትጠቀምበት እየተዘጋጀች ሲሆን) ወንዛችንን እንዳንጠቀምበት፣ ኢትዮጵያም እንዳታድግና እንዳትበለጽግ ጠላት ሆነው በመለመሏቸውና ባደራጇቸው አፍራሽ ሀይሎች አማካይነት በገንዘብና በጦር መሳሪያ እየረዱ የውስጥ ሰላማችንን እንድናጣ የሚያደርጉን ነው፡፡ ግበጽ ከጥንት ጀምሮ በተደጋጋሚ በተለይም ባለፉት 150 ዓመታት በተዳጋጋሚ ወረራ ለማድረግ ሞክረው ሁሉም ከሽፎባቸዋል፡፡ አሁንም  በወቅቱ ለሀገራችን ስጋት እና እንቅፋት ለመሆን ከፍተኛ ሴራ እያሴሩብን ነው፡፡ ሱዳንም እንደዚሁ ተመሳሳይ ተግባር እየፈጸመች ትገኛለች፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ አገሩን ከጥቃት ለመከላከል ሁሌም ዝግጁ ነው፡ መንግሥትም ኃላፊነት አለበት፡፡ በራሳችን ወንዝ ለመጠቀም ማንንም አናስፈቅደም፡፡ ሀብታችንና ሙብታችን ነው፡፡

የጠላቶቻችን ዓላማቸው ግን በከፊል የሰመረላቸው ይመስላል፡፡ እንደ ካንሰር ህዋስ ጤነኛው እየተበላሸ ሌላውን እንደሚያጠቃ ሁሉ፤ የውስጥ ጠላቶች ሆነው ለጠላት የሚያገለግሉት አብረውን ኖረው ከራሳችን መሀል ወጥተው ሲያጠቁንና ለጠላት መሳሪያ ሲሆኑ አገር አፍራሽነታቸውን ቶሎ ለይቶ ለማወቅና ለመዋጋት ብዙ ጊዜ ፈጅብን፡፡ ይህ የጠላት ስራ ስር መስደድ የጀመረው ጣሊያን ኢትዮጵያን ዳግም በወረረችበት ጊዜ አንዱ ምቹ የሆነላቸው ወቅት ነበር፡፡ ሆኖም ግን ጀግኖቹ የኢትዮጵያ አርበኞች አገራቸውን ከጠላት ለማላቀቅና ነጻነታቸውን ለማስከበር እጅግ ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍለዋል፡፡ በ 5 ቱ የጠላት ወረራ ዘመን ወንድ፣ ሴት፣ ወጣት፣ ጎልማሳ፣ አዛውንት፣ እስላም ክርስቲያን ሳይሉ የኢትዮጵያ አርበኞች ዱር ቤቴ ብለው በዱር በገደሉ ሲዋጉ ያልከፈሉት መስዋዕትነት የለም፡፡ እነ አብረሃም ደቦጭና ሞገስ አስገዶም የጣሊያኑን ግራዚያኒን ልጅ መወለድ ለማክበር በተሰበሰበው ያጣሊያን ወታደሮች ላይ የቦንብ ጥቃት አድርሰው በተፈጠረው ግርግር የጣሊያን ፋሽስቶች በሶስት ቀን በቻ ከ30 ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያንን በአዲስ አበባ በጥይት፣ በእሳት በማቃጠል፣ በዶማና አካፋ በጭካኔ ጨፍጭፈው ገድለዋል፡፡ የካቲት 12 ቀን በኢትዮጵያ የሚከበረው የሰማዕታት ቀን ያንን በማሰብ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የቆየችውና የኖረችው በህዝቧ ተከላካይነት እና ከፍተኛ መስዋዕትነት እንጂ ከየትም መጥቶ አለመሆኑን ታሪክ ይነግረናል፡፡

በአጼ ኃይለሥላሴም ጊዜ ቢሆን በሀገር ወስጥ የተማሩትም ሆነ በውጭ ተምረው የተመለሱት ሀገራችንን ለማሳደግ በቅንነትና በታማኝነት ጠንካራ ተቋሞችን በመመስረት ኢትዮጵያን ለማሳደግና ዘመናዊ ለማድረግ ብዙ የጣሩ ሰዎች እንደነበሩ ማስታወስ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ከእንግሊዞች የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ለመላቀቅ የተማረው ትውልድ ሃላፊነቱን በመውሰድ እንደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ አየር መንገድ፣ አውራ ጎዳና፣ ጤና ጠበቃ፣ ትምህርት ሚኒስቴር ወዘተ.... የመሳሰሉ ተቋማትን መስርተው ለሀገራቸው የሚቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል፡፡  ሥርዓቱ ግን ኋላ ቀር ሆኖ ሀገሪቷም በድህነት ወለል በታች ሆና፣ መሬትም በጥቂት ባለሀብቶች እጅ ሆኖ 90 በመቶው አርሶ አደር መሬት የሌለው ደሃ አፈር ገፊ ሰለነበር፣ ዲሞክራሲም የሌለበትና የማይታወቅ በመሆኑ ሕዝብ መሰረታዊ ለውጥን ይፈልግ ነበርና ወቅቱን ጠብቆ የየካቲት 66 አብዮት ፈነዳ፡፡

**የ60ዎቹና 70 ዎቹ ወጣቶች የከፈሉት መስዋዕትነት**

በዘመናችንም ቢሆን ከ 45 ዓመት በፊት በኢትዮጵያ የመጣውን የየካቲት ሕዝባዊ አብዮት ተከትሎ የንጉሱ አገዛዝ ሲለወጥ መንበረ ስልጣኑን በጊዜያዊ ስም ይዞ አለቅም ያለውን ወታደራዊ አምባገነን አገዛዝን ለመፋለም የኢትዮጵያ ወጣቶች እጅግ ብዙ መስዋዕትነት ከፍለዋል፡፡ ወታደራዊ መንግስትም ለስልጣኑ ሲል እጅግ ዘግኛኝ የሆነ ፋሽስታዊ ስራዎችን ፈጽሟል፡፡ ሁሉም ዛሬ ታሪክን አየጣመመ ለመጻፍ እንደሚሞክረው ሳይሆን ከወታደራዊ አምባገነን ጋር የነበረው ፈልሚያ አንድ ትውልድ የጨረሰ ታሪክ ጥሎ አልፏል፡፡ **በዘመኑ የነበረው ወጣት ለሕዝብ የቆመ፣ የቆመለትን ዓላማ ለማሳከት ደግሞ ለህይወቱ የማይፈራ፣ የሕዝብና የአገር ፍቅር ስሜት ያንገበገበው ጀግና ትውልድ ነበር፡፡** ትግሉ ጸረ ፊውዳልና ጸረ ኢምፔሪያሊዝም መሆኑን አቋሙን አሳይቷል፡፡ ታሪኩ ወደፊት በሚመጥነው መልክ ይጻፋል እንጂ እንዲህ በቀላሉ የሚገለጽም አይደለም፡፡ አንዱ ለአንዱ የነበረው ፍቅር፣ ዲሲፐሊን እና ቆራጥነት ለጉድ የሚወራ ነበር፡፡ ቴክኖሎጂ ባለተስፋፋበት፣ መረጃና ቅስቀሳ አብዛኛው በእጅ ጽሁፍ ሌላወም በታይፐ ተጽፎ አደፍርስ በሚባል በቤት የሚሰራ የጽሁፍ ማባዣ መረጃ እየተሰራጨ በእግርና ሲያመችም በመኪና ረጅም ጉዞ እየተጓዘ የፋሽስቱን የመንግስቱ ኃይለማርያምን መንግስት ለመፋለም ብዙ ጥሯል፣ ተዋግቷል፣ ዱር ቤቴ ብሎ በጫካ በበረሃ ተፋልሟል፡፡ ብዙ ወጣትም የሕይወት መስዋዕትነት ከፍሏል፡፡ የዚያ ትውልድ ስራ የእናት ሆድ ዝንጉርጉር እንደተባለው በዚያው ዘመንም አገራቸውን የከዱ፣ የመገንጠል እና የጠባብነት አባዜ ያናወዛቸው ሻዕቢያ፣ ኦነግ እና ወያኔ የሚባሉ ጸረ ኢትዮጵያ ኃይሎችም በመንቀስቀሳቸው ከጠላት ጋር በጅምላ የ 60 ዎቹ ትውልድ እየተባለ የሚወቀሰው ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል እንደተባለው አለአግባብ መሆኑን ሊጤን ይገባዋል፡፡ በወቅቱ ስህተትም ቢሰራ እንኳን ከትግል ልምድ ማነስ፣ ሁኔታዎችን በአግባቡ ካለመገንዘብ የመጣ፤ በወቅቱ ከነበረው የዓለም ፖለቲካና በነበረው ተራማጅ በሚባለው ርዕዮት ዓለም ግራ ዘመምን በመከተል እንጂ በእምነት እና በሀገር ፍቅር ደረጃ ወደር የሌለው ትውልድ ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡

ለመሆኑ የ 60 ዎቹ 70 ዎቹ ትውልድ ነው አገር ያጠፋው እየተባለ ያለቦታውና ራሱን መከላከል በማይችልበት መድረክ የሚወረድበት፣የከፈለው መስዋዕትነት ሁሉ ተሰርዞ የሚወነጀልበትና የሚወገዝው ለምንድነው? አውጋዡስ ማነው? ለምንስ ዓላማ ማውገዝ ተፈለገ? እስቲ በጥቂቱ እንዳስሰው፡፡

የ 60 ዎቿ 70 ዎቹ ትውልድ ዓላማና ግብ ምን ነበር? ለምንስ ያ ሁሉ ትወልድ በህይውትና በአካል መስዋዕትነት ከፈለ? ትግሉስ ለምን ግቡን አልመታም?

**ያ ትውልድ** የተነሳው ለራሱ ጥቅም፣ ለስልጣን ወይም ለተለየ ዓላማ አልነበረም በግፍ ያለቀው፣ የተገረፈው፣ አካለ ጎደሎ የሆነው፤ወህኒ የከረመው እና ለስደት የተዳረገው፡፡ አዎን ያ ትውልድ መስዋዕትነት የከፈለው የ 1966 ሕዝባዊ አብዮት ዓላማና ግብ በወታደራዊ አምባገነናዊ አገዛዝ ተጠልፎ ትግሉ አቅጣጫውን ሲስት፤ የሕዝብን መፈክር ዓላማ አንግቦ በመነሳቱ ነበር፡፡ **ከነዚህም ወስጥ መሬት ላራሹ፣ የዲሞክራሲ መብት ያለገደብ ይከበር፣ የጾታ እኩልነት ይከበር፣ የሃይማኖትና የብሄረሰቦች እኩልነት ይከበር፣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይመስረት የመሳሰሉትን መሰረታዊና ሕዝባዊ ዓላማዎችን አንግቦ በመነሳቱ ነበር፡፡** እነዚህንም ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ ደግሞ መደራጀት ወቅታዊና አንገብጋቢ በመሆኑ ለኢትዮጵያ አዲስ በነበረው በተደራጀ የፖለቲካ ድርጅት ስር መሰባሰብ አማራጭ የሌለው መንገድ ነበር፡፡ ይህም ሲሆን መታየትና መገምገም ያለበት በዛሬ ጊዜና መነጽር ሳይሆን ከ47 ዓመት በፊት በነበረው የአለም የፖለቲካ ሁኔታ፣ በጊዜው በነበረው ርዕዮተ ዓለም፣ ንቃተ ህሊናና የሕዝብ አስተሳሰብ ነው፡፡  ሰለሆነም ያ ትውልድ በአጭር ጊዜ ንቃተ ህሊናውን አሳድጎ፣ ተደራጅቶ ራሱን ለሕዝብ ትግል ሲያሰልፍ ከፍተኛ የሆነ መስዋዕትነት እንደሚያስፈልግ ተገንዝቦና አምኖበት አዕምሮውን አዘጋጅቶ፣ ሕዝብን በማንቃት፣ በማደራጀት እና የተለያዩ የብዙኀን ማህበራትን በመፍጠር እና በቆራጥነት በመታገል ነበር፡፡ አብዛኛው ወጣት ከደሃ አርሶ አደር እና ዝቅተኛ ገቢ ከነበረው ሕብረተሰብ የመጣ በመሆኑ ረሃብና ጥማቱን ተቋቁሞ፣ በእግሩ እየተጓዘ፣ ትምህርቱንና ስራውን በመተው ነበር በትግሉ የተሳተፈው፡፡ በትግል መስመር ላይ የነበሩ ጓዶች አንዱ ላንዱ ያለው ፍቅርና መከበባር እስከ ሕይወት መስዋዕትነት ድረስ የሚከፈልበትና የዘለቀ ትግል ነበር፡፡  ያ ትውልድ በከተማም ሆነ በገጠር፣ በፖለቲካ ስራውም ሆነ በጫካ ትግሉ አምኖበት የገባበት በመሆኑ ምንም ያህል ከባድ ቢሆን፣ መስዋዕትነት ለመክፈል ወደ ኋላ የማይል ጀግና ትውልድ ነበር፡፡ በእስር ቤቱም ቢሆን ጓዱን ለማዳን የሰው ልጅ የማይችለውን ስቃይ ችሎ ቆስሎና ስጋው በስብሶ ተበጣጦሶ ይሞት ነበር እንጂ አሳልፎ የማይስጥ ትውልድ ነበር፡፡ ተገርፎ ቁስሉ ሳይድን አዲስ የተገረፈውን ቁስል የሚያክምና የሚንከባከብ ፍቅር የሞላበት

ትውልድ ነበር፡፡ ይህንን እንኳዋን ትውልዱ ገራፊውና ደርግ እንኳዋን ጀግንነቱን የሚገረምበት የማይከደው ነበር፡፡ ታዲያ ለሆዱ ያላደረ፣ ለሱስና ለባዕድ ባህል ያለተንበረከከውን፣ ለገንዘብ የማይገዛ፣ ለሕዝቡና ለሃገሩ ፍቅር ከቡር ሕይወቱ ለመስጠት የማይሳሳና እጅግ ብዙ ሰቃይና መከራን የተቀበለ፣ ሲገደል ያመነበትን ዓላማ መፈክር እያሰማ ለዘለዓለሙ ያንቀላፋውንና እንዲሁም ከመከራ የተረፈውን ያንን ትውልድ ያለ አግባብ ለመዝለፍ፣ ለማውገዝ አፋቸውን የማይከብዳቸው ስዎች ዛሬ ላለው ወጣት ትውልድ እውነቱን እንዳይረዳ ታሪክ የሚያጣምሙና እንዲያወግዘው የሚያደርጉ ሰዎች እነማን ናቸው? ምክንያትና ዓላማችውስ ምንድነው? ይህን በሚገባ ማወቅ እጅግ ትክክለኛ፣ ጠቃሚና አስፈላጊ ነው፡፡

በዚያ ትውልድ ግድያና ስቃይ የሚደስቱ የነበሩ ቦዘኔዎች፣ የቀበሌ ገራፊዎች፣ የደርግ አባሎች፣ ከደርግ ጋር ወግነው በቀጥታ ተሳታፊ የነበሩ  ካድሬዎች ይህን ወንጀላቸውን ለመደበቅና አብዛኞቹ ዛሬ በውጭ ዓለም የሚኖሩና ባገር ቤትም ያሉት በሚቻላቸው መንገድ ሁሉ ያንን ትውልድ ያወግዛሉ፡፡ በመጽሐፍ ታሪክ ጻፍን ብለው ወንጀላቸውን ሸፋፍነወና ከደው ያንን ትውልድ ይወነጅላሉ ያወግዛሉ፡፡ ለምን? በሕግና በታሪክ ተጠያቂ እንዳይሆኑ ነው፡፡ ወያኔ ደግሞ ጉዳቸውን ሰለሚያውቅ ፋይላቸውን ደብቆ ይዞ ያንን ትውልድ እንዲያወግዙ፣ ተጨማሪም ወንጀል እንዲሰሩ መጠቀሚያ መሳሪያ ያደረጋቸው እንዳሉ ይታወቃል፡፡

ሌላው በዚያ ትውልድ የትግል ዘመን ጠባብና ተገንጣይ ቡድኖች ዓላማቸውን ለማሳካት ያን ትውልድ ይወነጅላሉ ያወግዛሉ፡፡ ሻዕቢያ፣ ወያኔ/ሕወሓት፣ ኦነግ እና ሌሎችም ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው፤ ለኢትዮጵያ አንድነት፣ ለሕዝብ መብት እና ሕዝባዊ መንግሥት የታገለውን ትውልድ ያወግዛሉ ይወነጅላሉ፡፡ ወያኔዎች በትግራይ የነበረውን የኢሕአፓ ሰራዊት ወግተው በትግራይ ምድር እንዳይንቀሳቀስ ያስደረጉትና የወጉት በጸረ ኢትዮጵያ አቋማቸው ነው፡፡ ተገንጣይና ጠባብ ቡድኖች በሙሉ የዚያን ትወልድ ትግል ያወግዛሉ፣ ይወነጅላሉ፡፡

**ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት ለድርድር የማይቀርብ ወቅታዊና ወሳኝ አጀንዳ ነው**

ወያኔ ደግሞ ላላፉት 30 ዓመታት በዘርና በጎሳ ከፋፍሎ አገር ሲያጠፋ ቢቆይም ብዙ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን በህይወት መስዋዕትነት፣ በእስራትና በስቃይና በስደት ከፍለዋል፡፡ ወያኔ የሚፈራው ነገር ቢኖር **የዚያ ትውልድ የትግል መንፈስና ተመክሮ በዛሬው ትውልድ ወስጥ እንዳይስረጽ ዘወትር ያንን ትውልድ ሲወነጅሉና ሲያወግዙ ወጣቱንም ሲሰብኩና ሲደልሉ ኖረዋል፡፡**

ዛሬም በወጣት ተዋንያን፣ ፖለቲከኞች፣ ተማሪዎች ዘንድ የዚያ ትውልድ መንፈስ፣ ጀግንነት እና የሀገር ፍቅር እንዳያንሰራራ ሰርዐቱን እንዳይገረስስ በጥቅም፣ በድለላ እና በተሳሳተ ታሪክ እያሳቱት በሽታቸውን ሊያስተላፉበት፣ የዘር ከትባታቸውን ከትበው እናት ሀገሩን እንዲረሳ ለማድረግ ያልተቆጠበ ጥረት ማድረጋቸውን አላቆሙም፡፡ ኅወሓት 28 አመት ኢትዮጵያን ለማጥፋት ታሪክ ሲያጠፋ፣ ትውልድ ሲገድል፣ የውሸት ታሪክ ሲፈበርክ፣ ሕዝብን ከሕዝብ ሲያጋጭና ሲያለያይ፣ በክልል እና በቋንቋ ከፋፍሎ ሲያጋጭ ኖሩዋል፡፡ በአንድ ብሄረስብ ስልጣኑን፣ የሃገሪቱዋን ሀበት ሲመዘብርና ሲያጠፋ፣ ያሻውን ሲገድል፣ ሲያስር ቆይቷል፡፡

የሕዝብ ትግል ሲያይልና ወያኔን አልገዛም ብሎ አመጽ ሲያነሳና መውጫ መግቢያ ሲያሳጣው ደግሞ አሁንም የሀገሪቱዋን በዘርና በቋንቋ መከፋፈል በገንዘብና በወታደራዊ ሃይል ሲደግፉ የነበሩ የውጭ መንግስታት ደግሞ አስልጥነው ያቆዩትን ሰው ትግሉን እንዲጠልፍ አመቻችተው ባለተረኛው የኦህዴድ/ ኦዴፓ ፓርቲ ደግሞ ህወሓቶችን ገለል በማድረግ ሰርዓቱ ሳይቀየር በጥገናዊ ለውጥ ስም ስልጣኑን ተረክቦ አገሪቱዋን ማመሱን ቀጥሏል፡፡ በጣም በርካታ ስዎች እውነትኛ ማንነቱ ሳይረዱ በቃላት ሸንገላ ብቻ አምነውት ከአመት በላይ ሲደግፉት ቆይተው ማነነቱን ሲገነዘቡ ድጋፋቸውን ቢቀንሱም በቆራጥነት ለመታገል ሀሞታቸውን አፍሶት ግራ ተጋብተው ተቀምጠዋል፡፡ እወነቱ ግን ኢትዮጵያን ማጥፋቱን፣ ሰርዓቱ እንደነበረ መቀጠሉን፣ ኢኮኖሚውንና ቁልፍ ቁልፍ የፖለቲካ ስልጣኑን በባለተረኛው እጅ አስገብተው ለሕዝቡ ሌላ አጀንዳ እየሰጡ እነርሱ አገር የማጥፋት ስራቸውን ቀጥለዋል፡፡ ኢትዮጵያ የምትታወቅባቸውን ተውፊቶች በማጥፋት፣ መሬት በመቀራመትና ሁሉን የእኔ የማለት አባዜያቸውን ገፍተወበታል፡፡ ዛሬም ቱባ ቱባ የወያኔ ወንጀለኞችን ተጠያቂ ሳያደርጉ አንዳንዱንም መልሶ በመሾም ወንጀላቸውን ቀጥለዋል፡፡ ፍትሕ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ተካደች!

ዛሬ ደግሞ በገባው ወረርሺኝ በሽታ ስም አዋጅ አውጀው እነርሱ የፈለጉትን እያደረጉ ናቸው። ምርጫውም በመራዘሙ በቅርቡ ‘ሕጋዊነታቸው’ ማብቃቱን ቢያውቁም የሽግግር መንግሥት በማቋቋም ፋንታ ለእራሳቸው በሚያመቻቸው መንገድ ሁኔታዎችን እያመቻቹ መሆናቸው እየታየ ነው፡፡ ከድጡ ወደ ማጡ ይሏል ይህ ነው፡፡ ባለተረኛው የኦዴፓ አገዛዝ ራሱን ብልጽግና ብሎ ቢያውጅም አፈጣጠራቸው፣ ዓላማቸው፣ ስራቸውም ያው የተነሱበት አገር የማጥፋትና የዘረኛ አገዛዝን ማሰቀጠል ሰለሆነ ሲታገላቸው የነበረው ትውልድ ዛሬም መታገልና መጮህ ያለበት፤ ከሁሉም የተውጣጣ ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት በመመስረት ኢትዮጵያን ማዳንና ዲሞክራሲያዊ ሰርዓትን ማስፈን አማራጭ የሌለው አንድና አንድ መንገድ ብቻ ነው፡፡ መዘንጋት የሌለበት ሕገ መንግሥቱ የወያኔ፣ ሰልጣን አጨበርብሮና ሰው ገድሎ የያዘው ወያኔ፤ አብይን ጠቅላይ ሚኒስትር ያደረገው ወያኔ፣ ታዲያ የኢትዮጵያ ሕዝብ መቼ ነው መርጦ ያስቀመጠው? ኮሎኔል አብይ ሲገድል፣ ሲያስር፣ ሲሰልል፣ ሲያስቃይ የነበረው ወያኔ ስለላ መረብ ኃላፊ አልነበረምን? ታዲያ እንዴት ነው ሰልጣኑን አደላድሎ የለየለት አምባገነን ከመሆን ውጭ እንደ ድመት ተቅለስልሶ፣ ‘መደመር’ ‘ብልጽግና’ ብሎ አዲስ ጭምብል ለብሶ እውነተኛ ማንነቱን ደብቆ የለውጥ አሽጋጋሪ የሚሆነው? የዘር ጭፍጨፋን ያካሄደ መንግሥት አካል እኮ ነው! **ለውጡ** የህወሓትን ዘረኛ አምባገነን በኦፒዲኦ/ኦዴፓ/ አምባገነን መቀየሩ ብቻ ነው! እንዴት ይረሳል ወገን! እንበል ሀገር አስቸጋሪ ፈተና ውስጥ ሆና የሽግግር መንግሥት ማቋቋም አስቸጋሪ ነው የሚል ሃሳብ ከቅንነት አንጻር ቢነሳ እንኳን ሕዝብ እንዲወስን በነጻ እንዲመክርበት ተደርጎ ተቃዋሚዎች ሁሉ የተሳተፉበት እውነተኛ ብሔራዊ መፍትሄ ይፈለጋል እንጂ የኦነግን ፓርቲዎች ሁሉ ሰብስቦ ከዘረኛ ዘረኛን ለመምረጥ መሞከሩ አደገኛ አካሄድ ነው፡፡ ተቃዋሚውን ሁሉ በጅምላ አውግዞ ኢትዮጵያ ከአብይ ውጭ ሌላ አማራጭ እንደሌላት በግልበኝነት የሚሰጡ መግለጫዎችና ጭፍን ደጋፊነት ኢህአዴግን ዘላለማዊ ክማድረግ ወጭ ሌላ ትርጉም የለውም፡፡

ሌላው ምሁር ነን ባዮች በውጭ የሚኖሩ እና የጡረታ ጊዜያቸውን ለማመቻቸት ወይም ተጨማሪ ገቢ ለማግኘትና እንደልብ ገባ ወጣ ለማለት እንዲያመቻቸው የኮሎኔል አብይን አዴፓን ደግፈው 'የለውጥ ጥሩንባ የሚያስጮኹ'፣ በገንዘብና በማቴሪያል እንደግፍ ብለው በየሀገሩ ያሉ ኤምባሲዎች ደጋፊ መሆናቸውን ማረጋገጫ እንዲሰጧቸው አፈቅላጤ የሆኑ አድርባይ ግለሰቦች ሁለቴ እንዲያስቡና ከግል ጥቅም ይልቅ የሀገርን ጥቅም ማስቀደም የማይፈልጉ አስቸጋሪ የሆኑ ሰዎችን ለጠላት የሚያጎበድዱ ከመሆን ቢቆጠቡ ይሻላቸዋል። ሕዝብ ሲፈናቀል፣ ከቤቱ ሲባረር፣ ሲታሰር ሲገደል አንድም ቃል የማይተነፍሱ የአዛውንት ሎሌዎች ተግባር እጅግ አሳፋሪ ሲሆን፤ በአንጻሩ ደግሞ በውጭም ሆነ በሀገር ቤት ያሉ እድሜ ልካቸውን ሕዝቤ፣ ሀገሬ፣ ባሕሌ ብለው ወያኔን ሲቃወሙ የቆዩትን፣ እንደ ጥጃ ሲታሰሩ ሲፈቱ የኖሩትን፣ በአቋማቸው ጸንተው የሚታገሉ የተከበሩ ምሁራን እና አዛውንቶች ደግሞ ሊታወሱ ሊከበሩ ሊደገፉ ይገባል፡፡ የዘመኑ ወጣት ትውልድንም በጅምላ ሱሰኛ፣ ገንዘብ ወዳድ፣ የውጭ ባሕል አራማጅ፣ ለሀገር ግድ የሌለው ብሎ መፈረጅ እጅግ ስህተት ነው ምክንያቱም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወጣቶች ላለፉት 30 ዓመታት በየጊዜው የሕዝብን ጥያቄ በማንገባቸው በህይወት፣ በእሥራት፣ በግርፋት፣ በስደት እንዲሁም 'እንዲጠፉ' ተደርገው መስዋዕትነት ከፍለዋል፡፡ በ97 ዓ/ም ምርጫን ተከትሎ እንኳን ግንባር ግንባራቸውን በጥይት ተነድሎ በየመንገዱ ህይወታቸውን ያጡት፣ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ በብር ሽለቆ፣ በዝዋይ፣ በደዴሳ፣ በቃሊቲ እና በስውር እስር ቤቶች የተሰቃዩትን ታሪክ ለዘለዓለም በክብር ያስታውሳቸዋል። ለከፈሉት መስዋዕትነት ደግሞ ጊዜውን ጠብቆ ለውጥ መምጣቱ አይቀሬ ነው፡፡

ስለሆነም የ60 ዎቹ እና 70 ዎቹ ትውልድ ትግል ጥያቄ ዛሬም ህያው ነው፡፡ ጊዚያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይመስረት፣ የኢትዮጵያ ሉ ዓላዊነት ይከበር፣ የዲሞክራሲ መብት ይከበር ጥያቄም ዛሬም ሕያው ነው፡፡  ዛሬም የነዚህና ሌሎችም ተዛማች ዓላማና ግብ ሳይሳካ አርፎ የሚቀመጥ ትውልድ የለም፡፡ የዛሬው ትውልድ የዘረኝነት አገዛዝ መረረኝ በቃኝ ብሏል፡፡ ዘላቂው መፍትሔው አንድ ብቻ ነው፡፡ ከሕዝብ የተውጣጣ የሽግግር መንግሥት መመስረት የማንደራደርበት የሕዝብ ጥያቄ ነው፡፡ ጥቂት የኢትዮጵያ ጠላት መሳሪያ የሆኑ ግለሰቦች የሕዝብን መፈክር ቀምተው ስለለፈለፉ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ጥያቄን ያነሳን ሁሉ በዚያ አይን መመልከት አይቻልም። ምክንያቱም ዘለቄታዊ ሰላም ሊሰፍን የሚችለው ሕዝብ የራሱን መንግሥት ሲመሰረት ብቻ ነው! ዘረኝነት አምባገነንነት ማክተም አለበት!፡፡

**ምን መደረግ አለበት?**

ከሁሉም በላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ መብት ተከብሮ፣ ዲሞክራሲ ሰፍኖ፣ ከድህነት፣ ኋላ ቀርነትና በሽታ ተላቆ ሀገራችን ልታድግ የምትችለው የሕዝብ መንግሥት ሲመሰረትና ሲኖራት ብቻ ነው፡፡ ባጋጣሚም ሆነ በጉልበትና መሳሪያ ወይም በተቀነባበር የውጭ ኃይሎች ሴራ ስልጣን ላይ የወጣ ሁሉ በሕዝባዊ አመጽ ወይም በሌላ አምባገነን መገርሰሱ አይቀሬ ነው፡፡ በኢትዮጵያም ከ1966 ዓ/ም ጀምሮ በተደጋጋሚ የሕዝብ መንግሥት ሳይመሰረት ይኸው 46 ዓመታት አለፉ፡፡ በተለይም ላለፉት 30 ዓመታት በሻዕቢያ፣ ሕወሓት እና ኦነግ አገራችንን በማፈራረስ ተግባር ላይ ተሰማርተው ብዙ ጥፋቶችን አድርሰዋል፡፡ ከአሁን በኋላ ግን  ያ እንዳይቀጥልና የማንመለስበት ጥፋት ደረጃ ከመድረሳችን በፊት ኢትዮጵያዊው ሁሉ ማድረግ ያለበትን ለመጠቆም እንወዳለን፡፡

በቅድሚያ ሀገርን የማዳን ያህል ዐብይ ጉዳይ ለመፈጸም በግለሰብ ደረጃ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚቻል ቢሆንም፣ በተደራጀ ኃይል ሲፈጸም ግን ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል ለማቀፍና ለማንቀሳቀስ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመፈጸምና ስኬታማ ደረጃ ላይ ለመድረስ መደራጀት የመጀመሪያው ደረጃ ስለሆነ መደራጀት ያስፈልጋል፤ የተደራጁም ኃይሎች ዓላማቸውን ግልጽ አድረገውና ወስጣቸውን ፈትሸው ተጠናክረው በኢትዮጵያ አንድነትና ሰላም ከሚያምኑ ኃይሎች ጋር ተነጋግረውና ተሰባስበው ኃይላቸውን ማቀናጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ያልተቀናጀ ትግል የጨረባ ተዝካር ከመሆን እንደማያልፍ በተደጋጋሚ ታይቷልና፡፡ ስለሆነም መሰባሰብ፣ መደራጀት ባጋራ መቆም የመጀመሪያው አስቸኳይ ተግባር መሆን አለበት፡፡ ኢትዮጵያ የሁሉም ዜጎቿ ሀገር እንደመሆኗ ሁሉ፤ ሰላሟም ሲደፈርስ ሆነ አደጋ ሲመጣባት ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል የሚዳስስ፣ የሚነካ፣ የሚመለከት በመሆኑ ሁሉም ዜጋ ለሀገሩ ሰላምና እደገት፣ ዲሞክራሲ መስፈንና ማደግ አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በፖለቲካ ድርጅት፣ በሙያ ማህበራት፣ በብዙሐን ማህበራት ውስጥ መደራጀትና መሳተፍ የሕበረተሰቡን አጠቃላይ ተሳትፎ የሚያካትትና ድምጻቸውን ለማሰማት ተጽዕኖም የሚፈጥሩ ኃይሎች ይሆናሉ፡፡ ቀደም ያሉት አባቶቻችን አገር ሲወረር፣ አደጋ ሲመጣ ሁሉም ተረባርቦ እንደሚወጣው፣ ባላፉትም ዓመታት የኢትዮጵያ ጀግኖች ልጆች በአርበኝነትም ሆነ በትግሉ ለሀገርና ለሕዝብ ፍቅር ሲሉ እጅ ለእጅ ተያይዘው እንደታገሉት፣ ሰማዕት እንደሆኑት፣ ለሀገራቸው እድገት አስተዋጽኦ እንዳደረጉት ዛሬም እጀ ለእጅ ተያይዘን፣ በአንድነት ቆመን የወስጥ አምባገነኖችን ካስወገደን፤ ተያይዘን ደግሞ የጥንት አባቶቻችን ኢትዮጵያን እንዳስከበሩዋትና ስሟን እንዳስጠሯት ሁሉ፤ እኛም ከውጭ ጠላቶቻችን አገራችንን ጠብቀን የቀድሞ ስሟን የማንመልስበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ በቅድሚያ ግን በውጭ ኃይሎች ፍላጎትና ግፊት ላያችን ላይ የተቀመጠብንን ዘረኛ አምባገነን አገዛዝ በሕዝብ መንግሥት መቀየር አንድና አንድ የማይባል ተግባር ነው፡፡ የትኛውም አምባገነን አገዛዝ በፈቃዱ ሥልጣን አይለቅም፤ እኛው ነን ማስለቀቅ የምንችለው፡፡ በገንዘብ ኃይል፣ በጉልበትና በሚዲያ ከፍተኛ የሆነ ጫና ለማሳደር፣ አድርባይ፣ ፈሪና ሆዳም ታዋቂ ግለሰቦችን ከፊት ለፊት በማሳየት መጠቀሚያ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን መገንዘብ፣ የስነ ልቦና ጫና ለማሳደር በገንዘብ በተገዙ የተለያይ ሚዲያዎች አንድ አይነት ዜናና ቅስቀሳ እንደሚያደርጉ በዚያ ሆያ ሆዬ ደግሞ ግራ ላለመጋባት መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡ ስለሆነም የአምባገነኖች ኃይል ጉልበት፣ ገንዘብና መሳሪያ ብቻ ነው፡፡ ከእነዚህ ሁሉ ኃይለኛው ግን የሕዝብ ኃይል ነው፡፡ ያንን መቋቋም ማሸነፍ የሚችል አምባገነን የለም! እስከዛሬም ስንሰቃይ የቆየነው በሚገባ የተደራጀ የሕዝብ ኃይል ሰላልፈጠርን ብቻ ነው፡፡ የ97 ምርጫን ስንመለከት ያንን ያህል ስራ የተሰራው ሕዝብ ስለተደራጀ ነበር ሆኖም ግን የተደራጁት ኃይሎች አስቀድመው ውስጣቸውን ፈትሸው ቢሆን ኖሮ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ለመሸሽና ለመፈርጠጥ ተዘጋጅቶ እንደነበር የትላንት ትዝታችን ነው፡፡ ዛሬም ማድረግ እንችላለን! ይህን ካልን ዘንዳ ወደተግባር ለመግባት ዛሬ ነገ ማለት ለጠላቶቻችን ጊዜ መስጠት ይሆንብናልና ወደ ሥራ ለመግባት እንነሳ! እንስራ፡፡ እውነተኛ ለውጥን እናምጣ፡፡ ይቻላል!

ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆቿ ታፍራና ተከበራ ለዘላለም ትኖራለች!